አቶ መለስ 25/10/ 06 ከሮይተር  አንደሪው ካውቶርን ጋር ባደረጉት ቃለ መጠየቅ

<u>በእናታቸዉ ኤርትራዊ መሆናቸውና አሰያስም እሱ የተወለደበት አካባቢ መወለዳቸውን አምነዋል። የነዚህ ዘመዶሞች የሜጩሻ ግብ ምንድነው? ጎበዝ ንቃ ሥራቸውን ተከታተል።</u>

እንዴት በኛ ጊዜ እንዴት በኛ   ዘመን
ኢትዮጵያ ስትጠፋ ቆመን እናያለን።

ተቆርጦ አንገታችን ተጥሎ ቀይ ባህር
ሌላው አካላችን በመለስ ሲመተር።
ሌት ተቀን ሲተጋ ሲበታትነን
አደራ ሲወጣ  የእናት ሀገሩን።
ምንድነው ዝምታ ጀሮ ዳባ ማለት
ህዝቡ ሲጨፋጨፍ በወያኔ ጥይት።
ይህንን ፍራቻ ማነው ያስተማረን
ኢትዮጵያ ስትጠፋ በአይናችን እያየን።

እንዴት በኛ ጊዜ እንዴት በኛ ዘመን
ኢትዮጵያ ስትጠፋ ቆመን እናያለን።

ታሪክህን መርምር የአባቶችህን
ሙሉዋን ኢትዮጵያ ያስረከቡህን።
መይሳው ካሳ ምኒልክ ዮሐንስ
መስዋዕት የሆኑ እነ አቡነ ጴጥሮስ።
ፈሰሰ እንባቸው ዛሬ ከመቃብር
ባንዳዎች ተቀምጠው በክብራቸው ወንበር።
እንዴት ነው የሚገዙ መለስ ኢትዮጵያን
በግልፅ ነግረውን አገራቸውን የቆሙላትን ኤርትርያን።

እንዴት በኛ ጊዜ እንዴት በኛ ዘመን።
ኢትዮጵያ ስትጠፋ ቆመን እናያለን።

አፈረ አሉላ ተሸማቀቀብን
ገብርዬ ተቆጣ በእኛ አዘነብን።
መቅደላ ተራራ ዛሬ ተናወጠች
መይሳውን ካሣ ካልተፋሁ እያለች።
ታሪክን እንመርምር ወደ ኋላ ዞረን
የመለስ አያት ነው ለእንግሊዝ የሸጠን።
የባንዶቹ ልጅ ኤርትራዊው መለስ
እንዴት ነው በኢትዮጵያ የሆነብን ንጉስ።

እንዴት በኛ ጊዜ እንዴት በኛ ዘመን።
ኢትዮጵያ ስትጠፋ ቆመን እናያለን።

ነጭ ወዳጆቻችን ድሮ ያልቻሉን
በታንክ በአውሮፕላን የተሰለፉብን።
ኤርትራውን መለስ ከላያችን ጭነው
በቤት በጓዳችን ዛሬ አዛዥ ሆነው።
በምዕራብ በምሥራቅ በደቡብ በሰሜን
እሳት ሲለኩሱ ለማጥፋት ሀበሻን

ምንድነው ዝምታ ዛሬ በእኛ ዘመን።
የጥንቱ ህልማቸው ሰፈፀም እያየን
የአባቶቻችንን ደም ምነው አቀለልነው?
ለጥቁር ሕዝብ ሁሉ መመኪያ የሆነው።

እንዴት በኛ ጊዜ እንዴት በኛ ዘመን
ኢትዮጵያ ስትጠፋ ቆመን እናያለን።

መቼ ነው ክርስቲያን የተጣላው ከእስላም
በውዲቷ ኢትዮጵያ በሀገረ ሰላም።
መቼ ነው ነጮቹ እንዲህ የደፈሩን
ገንዘብ እየሰጡ የሚያስጨፈጭፉን።
ጆሮ ያለው ይስማ ይገለጥ አይንህ
እንግዲህ እወቀው ቅኝ ተገዥ ነህ።
እናት አባቶችህ ያንተ ታናናሾች
ሆነዋል እንግዲህ የነመለሰ ባሮች።
ልጆችም ብትወልድ ሀገር የሌላቸው
ሲያፍሩ ይኖራሉ በእናት በአባታቸው።

እንዴት በኛ ጊዜ እንዴት በኛ ዘመን
ኢትዮጵያ ስትጠፋ ቆመን እናያለን።

አፋቸው ኢትዮጵያ ሚሸጡን ለነጮች
መለስ ጓደኞቹ የእኛ ቅኝ ገዢዎች።
በብሔር በጎሳ ከፋፍለው እኛን
ቆርጠው የተነሱ ሊያጨፋጭፉን።
ክርስትያኑን ከእስላም ሊያገዳድሉት
በምሥራቅ በምዕራብ እሳት ሚጭሩት።
ምንድነው አላማው ወዴት ነው ግባቸው
ኢትዮጵያን ማጥፋት ነው የቀን ቅዠታቸው።

እንዴት በኛ ጊዜ እንዴት በኛ ዘመን
ኢትዮጵያ ስትጠፋ ቆመን እናያለን።

ዛሬ ተነገረን ለእኛ በድፍረት
የመሪዎቻችን ኤርትራዊነት።
የአያቶቹን ጅምር ከግቡ ለማድረስ
ደፋ ቀና ሲል ኢትዮጵያን ለማፍረስ።
ለነሱ አላማ እኛ ተመቻችተን
ፖለቲካ እያልን ከሀገር እርቀን።
አልሰማንም እኛ ጆሮ ዳባ ብንል
የአባቶቻችን ደም ይፋረደናል።
እረፍት ይነሳናል እስካለን በሕይወት
ፍርድ ይጠብቀናል ደግሞም በሰማይ ቤት።
በምድር የታሰረ በላይ አይቀርለት
መፈፀሙ አይቀር የጴጥሮስም ግዝት።
ደሙን ያፈሰሰው በመትረየስ ጥይት
ለኢትዮጵያ አንድነት ለኢትዮጵያ ነፃነት።
ለእኛ ክብር ኩራት።

የአጽብአ - በርን - ስዊዘርላንድ